# ጭንጋፍ ፣ የንግዴ ልጅ

በጠባቦች ሴራ ፣ ፈሪ በትራቸው
የአማራን አመራር ፣ ድንገት ያረዳቸው
ሆድ ሲያውቅ ፣ ዶሮ ማታ ፣ ሆኖ ገዳያቸው
መፈንቅለ መንግሥት ፣ በሚል ተረታቸው
ገሎ ለቅሶ ደራሽ ፣ ጭምብላም ገድላቸው
ሕዝብ አልቀበል ሲል ፣ ሲጋለጥ ስራቸው
ተጠናከረው መጡ ፣ በአፈናና እስራቸው
በሰፈሩት ቁና ፣ አንተም ስፈራቸው ።

ለሌላው ጨልሞ ፣ ለሱ ቀን የወጣ
የመሰለው ከንቱ ፣ የሰላም ጋሬጣ
በከንቱ መጀነን ፣ እንደማያዋጣ
ቀፎውን ነካከተህ ፣ ሕዝብ ሳታስቆጣ
በሰፈርከው ቁና ፣ መስፈር ሳይመጣ
ከመንደር ምሽግህ ፣ ከጥበትህ ውጣ
መሸሸጊያም የለህ ፣ አማራው ሲቆጣ ።

ትንሹም ትልቁም ፣ በትዕቢት ያበጠ
በማንም ተረኛ ፣ ምራቁን ባልዋጠ
በአማራ ስቃይ ፣ እየተላገጠ
ሰላሙን ተነሳ ፣ ኑሮው ተናወጠ
መመለሻም የለው ፣ ፍኖው ከቆረጠ
ባመቱ ይውጣል ፣ ጀግናው ባላመጠ ።

የፅንፈኛው መንጋ ፣ በለመደ አመሉ
አማራን ማሳደድ ፣ አማራን መግደሉ
ከእንግዲህ አይሰራም ፣ እንዳትከጅሉ
ማገዶ ሳትፈጁ ፣ ይበጃል ብትበስሉ
ሶስት አራቱ አስቡ ፣ ቁሙና አስተውሉ
በሕዝቡ ማዕበል ፣ ቁጣ ሳትበሉ ።

ጋንግሪን የሆነ ፣ ቁስላቸው የማይድን
በራስ ለመመካት ፣ ያልታደሉ ምስኪን
አረም የበቀሉ ፣ ባገር የተነዙ
ጋኔል የሚጠሩ ፣ በየ ወንዛ ወንዙ
ወርቅ ላበደረ ፣ ጠጠር እየሰጡ
ከመቃብር ደጃፍ ፣ ሞት ሲቀላውጡ
አንበሳን ነካክተው ፣ ይቀሰቅሳሉ
መቀበሪያቸውን ፣ ጉድጓድ ይምሳሉ ።

እንኳንስ ለራሱ ፣ ላገር የሚዋጋ
የአድዋን የማይጨው ፣ ታሪክ አትዘንጋ
ጭንጋፍ የንግዴ ልጅ ፣ የመናፍቅ መንጋ
ለመውደቅ አትቸኩል ፣ ትንሽ ተረጋጋ
ለጊዜው ነው እንጂ ፣ አልጋውም አይረጋ
እነ ሁሉም ኬኛ ፣ ይከፍሏታል ዋጋ ።

ታዛቢው

July 24, 2019